የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

Media Digest
ሚዲያ ዳሰሳ

ለግሉ ዘርፍ ወቅታዊ የቢዝነስ መረጃ ለማቀበል እንተጋለን

We strive to nurture private sector with latest business tips

በተለያዩ የህትመት ሚዲያዎች ላይ ከሚወጡ የቢዝነስ ዘገባዎች ውስጥ የተመረጡ ጽሁፎች የሚተነተኑበት ገጽ

በመረጃና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ
(መጋቢት 15 ቀን 2012 ዓ.ም.)

Article analysis on selected business reports

A bimonthly issue under Information & Capacity Building Directorate
(March 24 2020)

# ኮቪድ-19 በኢኮኖሚው ላይ እያመጣ ያለው ተፅኖ

*ኮቪድ-19 ተብሎ እየተጠራ ያለው የኮሮና ቫይረስ በቻይና ወሃን ግዛት ከተቀሰቀሰ ጀምሮ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገሮችን በማዳረስ ዘርና ሀይማኖትን ሳይመርጥ የሰዉ ልጆች ሁሉ እያጠቃ ይገኛል፡፡ የበርካታ ሰዎችን ጤና ከማቃወሱና ህይወትን ከመቅጠፉ ባሻገር የቢዝነስ እንቅስቃሴን በማዳከም የሀገራት ኢኮኖሚንም እያደቀቀ ነው ፡፡ ቫይረሱ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ለንባብ ከበቁት ሚዲያዎች ሁለቱ ይዘው የወጡትን ዘገባ እንደሚከተለው በትንታኔ ተመልክተነዋል፡፡*

## *ፎርቹን*

ፎርቱን ጋዜጣ በማርች 22 2020 ዕትሙ ገጽ ሁለት ላይ “COVID-19 Hits Some Businesses Hard, Yet Blesses Others” በሚል ርዕስ ሥር ባወጣው ዘገባ የኢትዮጵያ መንግሥት በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የቫይረሱ ተጠቂ የ48 ዓመት ጃፓናዊ መጋቢት 5 ቀን 2012 ዓ.ም. ይፋ ማድረጉን ተከትሎ በመዲናዋ በርካታ እንቅስቃሴዎች እየተገቱ መጥተዋል ሲል ያስነበበናል፡፡ ዘገባው በመቀጠልም ይህ የእንቅስቃሴዎች መቀነስም በኢኮኖሚው ላይ ግልጽ ተፅዕኖም ማምጣት ጀመረ ሲል ይዘግባል፡፡ ወረርሽኙን ለመከላከልም የኢትዮጵያ መንግስት300 ሚሊዮን ብር መመደቡን ሲያስታውቅ፣ የአለም ባንክ 121 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ያደረገ ሲሆን የንግድ ባንክ ደግሞ 10 ሚሊዮን ብር ለመለገስ ቃል መግባቱንም ይጠቅሳል፡፡ የኢትዮጵያ ጤና ተቋም 200 የሚሆኑ የጤና ባለሙያዎችን በመመደብ በተለይም ቫይረሱ ካጠቃቸው አገሮች የሚመጡ ተጓዦችን እየመረመረ እንደሚገኝም በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ አደገኛ ቫይረስ በአለም አቀፍ ደረጃ ከ11 ሺ የሰዎች ሞት እና በኢትዮጵያ ደግሞ ሰዎች በበሽታው የተያዙ መሆናቸው ሲሰማ በተለይም በአዲስ አበባ የቢዝነስ ድርጀጅቶች እንቅስቃሴ መቀዝቀዙ እና በኢኮኖሚያቸውም ላይ አሉታዊ ተጽኖ ማምጣቱ ተስተውሏል፡፡ ቫይረሱን ለመከላከል ለሚደረገው ቅድመ ዝግጅት በሚገዙ ቁሳቁሶች እና ባህላዊ ምግቦች ምክንያት መድሀኒት ቤቶች፣ ግሮሰሪዎች እና መሰል ድርጅቶች ቢጨናነቁም እንኳ ጥቂት የማይባሉ የቢዝነስ ድርጅቶች የደንበኞቻቸው ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት የሚያቀርቡት ምርቶችና አገልግሎቶቻቸው በሚፈለገው መጠን ባለመሸጣቸው በእለት ተለት ገቢያቸው ላይ ተጽኖ አሳድሯል፡፡ በተለይም የቫይረሱን መስፋፋት ለመከላከል በተቋቋመው ኮሚቴ አማካኝነት ማርች 16/2020 በተላለፈው መልዕክት መሰረት ከመንግስት ዩንቨርስቲዎች በስተቀር ሁሉም ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ፣ ትልልቅ ስብሰባዎች እንዲሰረዙ እና በርካታ ሰዎች የሚገኙባቸው እንደ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች በጊዜያዊነት ለሁለት ሳምንት በመሰረዛቸው ምክንያት ሆቴል ፣ ሬስቶራንቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ሲኒማ ቤቶች እና ጅም ቤቶች የመሳሰሉት ድርጅቶች ገቢያቸው መቀነሱን ፎርቹን ባለቤቶቹን ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

በብዛት የውጭ እንግዶችን ሲያስተናግዱ የነበሩ ሆቴሎች ቫይረሱ ባመጣው ጣጣ ደንበኞቻቸውን በማጣታቸው ክፉኛ ተጎድተዋል፡፡ ፎርቹን ለአብነት ቃለ መጠይቅ ያደረጋቸው በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የካፒታል እና ጁፒተር አለም አቀፍ ሆቴሎች ፤ እንዲሁም የጣይቱ ሆቴል በቫይረሱ መከሰት ምክንያት የደንበኞቻቸው ቁጥር የቀነሱባቸው እና ገቢያቸው እያሽቆለቆለባቸው ካሉት ውስጥ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ቦሌ ሮክ የአካል ብቃት ማዕከል እና አለም ጂም በበኩላቸው ደንበኞቻቸውን ከማጣታቸው የተነሳ በከፍተኛ ደረጃ ገቢያቸው እየቀነሱ ካሉ ድርጅቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ በሰዎች ትፍፍግና ንክኪ ለተጋለጡ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ እንዚህን የመሰሉ ድረጅቶችን ጨምሮ እንደ ባህላዊ ጭፈራ ቤቶች፣ የሳዉና፣ የማሳጅ እና የመዋቢያ አገልግሎት የሚሰጡም ከፍተኛ ኪሳራ የደረሰባቸው በመሆናቸው ሰራተኞቻቸውን የዓመት ረፍት እንዲወጡ ከማስገደድ ባለፈ ቅነሳ እስከ ማድረግ የደረሱ ናቸው፡፡ መንግስትም ሆነ የትኛውም የህብረተሰብ ክፍል አስፈላጊውን ሀላፊነት በመወጣትና ጥንቃቄ በማድረግ ቫይረሱ በቶሎ በቁጥጥር ስር ካልዋለ ከዚህም የባሰ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡

158 አገሮች የቫይረሱ ወረርሽኝ የደረሰባቸው እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን ኢትዮጵያም በምስራቅ አፍሪካ ካሉ አገሮች በ3ኛ ደረጃ የቫይረሱ ተጠቂ መሆንዋን በጤና ሚኒስቴር አማካኝነት በተገለፀ ወቅት ነዋሪው የበሽታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ የሚችለውን ሁሉ በማድረግ ቫይረሱን ይከላከልልኛል ብሎ የሚያምንባቸውን እንደ ሎሚ ፣ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል ያሉ ባህላዊ ምግቦችንና መድሀኒቶችን እንዲሁም አልኮል፣ የአፍንጫና የአፍ መሸፈኛዎች፣ እና ጓንት የመሳሰሉትን ዘመናዊ መከላከያዎችን ለመግዛት በሚያደርገው ርብረብ ስግብግብ ነጋዴዎች እየጣሉባቸው ባለ እጅግ የተጋነነ ዋጋ ህብረተሰቡን ለአላስፈላጊ ወጪ ሲዳርጉት ይታያል፡፡ ይህን ተከትሎ መንግስት አዲስ አበባን ጨምሮ በኦሮሚያና፣ በአማራ ፣ ሶማሌ፣ ድሬደዋ፣ ቤንሻንጉል ግሙዝ እና ሌሎች ክልሎች በሚገኙ በርካታ ህገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ እየወሰደ ይገኛል ይለናል ፎርቹን በዘገባው፡፡

ይህ ድርጊት በህጋዊ፣ በባህላችንም ሆነ በሰብአዊነት ውግዝና ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ በእንደዚህ አይነቱ አስከፊ ችግር ወቅት ወገን ለወገን በመተሳሰብና በመረዳዳት ሊተካ የማይችለውን የሰው ልጅ ህይወት ለማትረፍ መረባበረብ ይገባዋል እንላለን፡፡

# ሲቢሲ -ቢዝነስ ኢንሳይደር

ሲቢሲ-ኮሜሳ (የኮሜሳ ቢዝነስ ካውንስል) “Business Insider” በሚል ርዕስ ሥር የሚያሳትመው ኢ-ኒውስሌተር በልዩ ዕትሙ ላይ «BUSINESS INSIGHTS OF THE COVID- 19 VIRUS» በሚል ርዕስ ተመሳሳይ ዘገባ ይዞ ወጥቷል፡፡ ቫይረሱ በሰዎች ኑሮ፣ ኢኮኖሚ፣ ገበያና ንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እያደረሰ መሆኑን በመግቢያው ላይ ያስነበበን ዘገባው፤ ወቅታዊ ሁኔታዎች እንደሚያመለክቱት ከሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር ተፅዕኖው በአፍሪካ አነስተኛ ቢሆንም አህጉሪቱ ከቻይናና ከአውሮፓ ጋር ካላት የገበያ ትሥሥር አኳያ ሲለካ በሁሉም ዘርፎች ላይ ሊታይ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ውድቀት ቀላል የሚባል እንደማይሆን የተባበሩት መንግሥታት የንግድና ልማት ጉባዔን (ዩኒክታድ) በመጥቀስ ያትታል፡፡ እንደ ዩኒክታድ መረጃ አሁን ባለው ሁኔታ የኮረና ቫይረስ የዓለምን ኢኮኖሚ እስከ 2 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ የሚያስከፍል ነው ቀጣይ ስጋቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡፡ በዚያ ላይ እያሽቆለቆለ የሚሄደውን ኢኮኖሚ ለመታደግ እየተወሰደ ያለውን እርምጃ አስመልክቶ ግልጽ ነገር የለም፡፡

**በአፍሪካና በኮሜሳ የሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ፡-**

*የመጀመሪያው የወረርሽኙ ምልክት በአፍሪካ በግብጽና አልጄሪያ ከታየ ጊዜ አንስቶ ወደ 33 በሚጠጉ ሀገሮች መዛመቱን የተመለከተው ዘገባው ሠራተኞች በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው ሥራቸውን የመሥራት፣ በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ አለመገኘት፣ የትምህርት ቤቶችና የህዝብ ስብሰባዎች ላልተወሰነ ጊዜ መቆም የመሳሰሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች መታወጃቸው በኢኮኖሚው ላይ የመቀዛቀዝ አዝማሚያን እያሳየ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የኮሜሳ ዓለም አቀፍ የንግድ አጋሮች የሆኑት ቻይና፣ የአውሮፓ ህብረት የተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶችና አሜሪካ በኮሜሳ ንግድ ውስጥ መሪ ተዋንያን ናቸው፡፡*

*ቻይናና የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት የማኑፋክቸሪንግ ማዕከላትንና ወደቦችን ከመዝጋት ባለፈ የሰዎችን ዝውውር ማገዳቸው ለኮሜሳ ምርቶች ያለው ፍላጎት እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ የነዚህ አገራት አስመጪዎችም በወደቦች መዘጋትና በዜጎች የፍጆታ መቀነስ ሳቢያ ትዕዛዞችን ያቆሙ ሲሆን የኮሜሳ አባል ነጋዴዎች ምርቶቻቸውን ባሉበት ቦታ ሁሉ በቅናሽ ዋጋ እንዲለቁ ተገደዋል፡፡ ኮሜሳ ወደነዚህ አገራት የሚልካቸው ምርቶች ጠቅላላ ዋጋ በአውሮፓ ህብረት 49፣ በቻይና 15፣ በተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች 8 እና በአሜሪካ 6 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን መዳብና የመዳብ ሽቦዎችን የመሳሰሉ የማዕድን ምርቶች፣ ነዳጅና የነዳጅ ማጣሪያ፣ የባይቲሚኑስ ቁሶች፣ ቡና፣ አበባ፣ አልባሳት፣ ጀርሲዎች፣ የአሣ ምርቶች፣ የወይራ ዘይት፣ ካልሲዎች፣ ወርቅ፣ እንዲሁም በርካታ የፍራፍሬና ሌሎች የብረትና ማዕድን ምርቶች መሆናቸው በዘገባው ተጠቅሷል፡፡*

*ባንፃሩ ኮሜሳ ከአውሮፓ ህብረት የ54፣ ከቻይና የ33፣ ከተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች የ12፣ ከህንድና ከደቡብ አፍሪካ ከያንዳንዳቸው የ11 ቢሊዮን የኤሜሪካ ዶላር የኢንዱስትሪ ማሽሪዎችን፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ የትራንስፖርት መሣሪያዎችን፣ የጨርቃጨርቅ፣ አውቶሞቢሎችን፣ ብረት፣ የነፍሳት መድኃኒት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ሰልፈር፣ መድኃኒቶችን፣ ስንዴ፣ ኬብሎችን፣ ኤርክራፍት፣ ትራክተርና የህክምና መገልገያ ምርቶችን ገቢ የሚያደርግ ሲሆን በወረርሽኙ ተፅዕኖ ሳቢያ በወጪም ሆነ በገቢ ምርቶቹ ላይ የገበያ መውረድን ለማስተናገድ ተገዷል፡፡ ከሁኔታው መረዳት እንደሚቻለው ወረርሽኙ የአቅርቦትና የገበያ ትሥሥሮችን በመገደብ የገቢ ምርቶች እጥረት እንዲፈጠር ስለሚያደርግ በቀጣይ ለኢንዱስትሪዎችና ለሸማቶች በሚቀርቡ ቁሳቁሶች፣ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ መናርን ሥጋት ይደቅናል፡፡*

*አፍሪካም እርስ በርስ በምታደርገው ግብይት በሎጂስቲክስ ወጪዎችና በትራንስፖርት ችግር ሳቢያ ውጥረት ውስጥ ገብታለች፡፡ የአየር ትራንስፖርት ላይ የተደረገው ማዕቀብ ዋነኛው እርምጃ ሲሆን የአየር ትራንስፖርት መሰረዝ የአየር መንገድ ኢንዱስትሪውን ብቻ ሳይሆን እንደ ቱሪዝም ያሉ ተያያዥ ኢንዱስትሪዎችንና የንግዱን አገልግሎት ጭምር ነው፡፡ መጽሄቱ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት ማህበርን ጠቅሶ እንደዘገበው በያዝነው ዓመት የአቪዬሽን ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ የ29 ቢሊዮን ዶላር፣ በተሳፋሪ-ኪሎሜትር ሲሰላ የ4.7ከመቶ የኢንዱስትሪ ገቢ ኪሳራ ያሳየ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአፍሪካ አየር መንገድ የ40 ሚሊዮን ገቢ አሳጥቷል፡፡ በአፍሪካ ሀገሮች መካከል በድንበር የሚደረግ መደበኛ ያልሆነ ንግድም በእንቅስቃሴ ክልከላው የተነሳ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ውድቀት ሥጋት ይስተዋላል፡፡ በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የሚደረገው መደበኛ ያልሆነ ንግድ ልውውጥ ለኮሜሳ የንግድ እንቅስቃሴ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ዘገባው ያትታል፡፡*

*ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የዩኒክታድ 2019 የዓለም ኢንቨስትመንት ሪፖርት እንደሚያመለክተው እ.ኤ.አ. የ2018 የአፍሪካ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰቱ 46 ከመቶ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ዋነኞቹ ኢንቨስተሮች ፈረንሳይ፣ ኔዘርላንድስ፣ አሜሪካና ቻይና ናቸው፡፡*

**ትኩረት የሚሹ ነጥቦች (የመፍትሄ አቅጣጫዎች)**

በቢዝነስ እና በኢኮኖሚው ላይ ለተፈጠረው ችግር ፈጣን እና ውጤታማ ርምጃ ለመውሰድ በግሉ ዘርፍም ሆነ በመንግስት የሚከተሉት እርምጃዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሲቢሲ-ኮሜሳ (የኮሜሳ ቢዝነስ ካውንስል) ይመክራል፡-

- የብሄራዊ ሴፍቲኔቶች (National safety nets) ማስፈለግ፡- በእንደዚህ አይነት አስከፊ ወቅት የግል ድርጅቶችን ቢዝነስ ለማገዝ ብሄራዊ ሴፍቲኔቶች ያስፈልጋሉ፡፡
- አማራጭ አገር በቀል ገበያዎች እና ቀጠናዊ ትስስር ያለው የንግድ አጋርነት/ትብብር ላይ ማተኮር
- በቤት ውስጥ በመሆን የመስራት፣ የዲጅታል ስብሰባዎችን በመጠቀም እና በመራራቅ የመስራት ስርዓትን የሚያጠናክሩ የቢዝነስ እቅዶች ላይ ማተኮር
- ነባሩን የቢዝነስ አሰራርዎን በመከለስ የድረጅትዎን ውስጣዊ አቅም እና ምርታማነት በማጠናከር በቫይረሱ ምክንያት በተፈጠረው ለአዲሱ የደንበኞች ፍላጎት ምላሽ መስጠት መቻል
- በወቅቱ በተፈጠረው የሀገር ውስጥ የገበያ ምርት እጥረትን ለመቅረፍ የሀገር ውስጥ ምርቶችን መጨመር ላይ ትኩረት ማድረግ
- ብድር የሚያገኙበትን እና እዳዎን በአግባቡ የሚመልሱበትን መንገድ ማመቻቸት
- የኮንትራት ግዴታዎች ለሚያስፈልጋቸው ውሎች ዝግጁ መሆን
- በባለድርሻ አካላት መካካል ትብብርን እና ግልፅ የሆነ ተግባቦትን መጨመር ፡- ወረርሽኙን ለመግታት መንግስት በባለድርሻ አካላት መካካል የግል ዘርፉን ጨምሮ ውጤታማ ተግባቦትን ማረጋገጥ ይገበዋል፡፡

***እኛም ጉዳዩ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ ምክክር የሚሻ ስለሆነ ም/ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ቢንቀሳቀስ በወረርሽኙ ሳቢያ ሥጋት የተጋረጠበትን የሀገራችንን ኢኮኖሚ መታደግ እንችላለን ብለን እናምናለንና ይታሰሰብበት ስንል መልእክታችንን እያስተላለፍን ለተጨማሪ መረጃ የሚከተሉትን ሊንኮች መጠቀም እንደምትችሉ እንጠቁማለን፡፡***

- **በኮሮና ቫይረስ ሥጋት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን መጎብኘት ተከለከለ**
- **ንግድ ባንክ ለኮሮና ተፅዕኖዎች የሚውሉ ድጋፍ ለገሰ**
- **የኢትዮጵያ አየር መንገድ በኮሮና ቫይረስ ቀውስ 190 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማጣቱን አስታወቀ**
- **በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት የሆቴሎች ገበያ 50 በመቶ ቀነሰ እና ሌሎችም በሚከተለው ሊንክ ማንበብ ይቻላል**

**(https://www.ethiopianreporter.com/bizines)**

- **ህብረቱ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ መከላከያዎች በማሰራጨቱ እየተወጣች ላለችው ሚና ምስጋና አቀረበ**
- **ኢትዮጵያ የኮሮናቫይረስ በአፍሪካ ኢኮኖሚያ ላይ የሚያደርሰውን ጫና ለመቀነስ የሚያስችል የድጋፍ ምክረ ሀሳብ ለቡድን 20 አባል ሀገራት አቀረበች**

**(https://fanabc.com/bizines)**